# የቤት ውስጥ ሰራተኛ
# የአገልግሎት ውል ናሙና

**የቤት ውስጥ ሰራተኛ አገልግሎት አሰጣጥ ውል (ናሙና)**

ኦክቶበር 1/2023 ተግባራዊ የሆነው የ2022 የቤት ውስጥ ሰራተኛ የስራ መብቶች ማሻሻያ ሕግ (ዲሲ. ሕግ 24-305፤ ዲሲ ኮድ § 32-1071.01 እና *ተከታታዮች*) ("ሕጉ") እንደ ሞግዚቶች፣ የአረጋውያን ወይም የአካል ጉዳተኞች ተንከባካቢዎች፣ የቤት ጽዳት ሠራተኞች፣ ምግብ ሰሪዎች እና አትክልተኞች ያሉ የቤት ውስጥ ሠራተኞች ስለ ሥራቸው ውሎች እና ሁኔታዎች ግልፅ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ መስፈርቶችን አስቀምጧል።

የሕጉ አንቀጽ 102 (ዲሲ. ኮድ § 32–1071.02) ቀጣሪ አካላት የስራ ውሎችን እና ሁኔታዎችን በዝርዝር የሚገልጽ የጽሁፍ አገልግሎት ውል ከቤት ውስጥ ሰራተኞቻቸው ጋር እንዲፈጽሙ ይጠይቃል። ይህንን ጥረት ለመደገፍ እና ሕጉን ከማክበር አንፃር የቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ የቤት ውስጥ ሰራተኛ አገልግሎት ውል ናሙና አዘጋጅቷል። ይህን ናሙና መጠቀም በሕጉ የሚጠየቅ ባይሆንም፣ በሚፈፀም የአገልግሎት ውል ውስጥ የሚፈለጉትን ሁሉንም ድንጋጌዎች ያካትታል። የቤት ውስጥ አሠሪዎች/የቅጥር ድርጅቶች እና የቤት ውስጥ ሰራተኞች የቅጥር ሁኔታዎችን በጋራ ለመረዳት ይህንን ናሙና የውል ስምምነት እንደ መመሪያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

**ይህ የስራ ውል ናሙና በቅጥር አገልግሎቶች መምሪያ የቀረበ የሕግ ምክር አይሆንም።** የቅጥር ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው ከፍተኛውን ጥበቃ የሚሰጥ ህግ ለመከተል የአካባቢውን እና የፌዴራል ህጎችን መመርመር እና እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የሕግ መስፈርቶችን በራሳቸው ውል ውስጥ ማካተት አለባቸው። አሁንም ቢሆን የቅጥር ድርጅቶች እና የቤት ውስጥ ሰራተኞች ተፈፃሚ ሕጎችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው።

በርካታ ሕጎች በግል ውል ሊተላለፉ የማይችሉ መብቶችና ጥበቃዎች አሏቸው። የቤት ውስጥ ሰራተኛ የአገልግሎት ውል ናሙና በፌዴራል፣ በስቴት ወይም በአካባቢ ሕግ መሰረት ያሉ የሰራተኛ መብቶችን ወይም ጥበቃዎችን አይሽርም። ስምምነቱ ለሚመለከተው አካል ከፌዴራል፣ ከስቴት ወይም ከአካባቢው ሕግ የተለየ መብት ወይም ጥበቃ ሊሰጥ ይችላል። ይህ ህትመት ለቅጥር ድርጅቶች እና ለቤት ሰራተኞች በፈቃደኝነት የሚቀርብ የመረጃ ምንጭ ለማቅረብ የታሰበ አጠቃላይ መረጃ ነው እናም ከኦፊሴላዊ የአቋም መግለጫዎች ጋር በተመሳሳይ መልኩ አይታይም። የዚህ የአገልግሎት ውል ናሙና ይዘት የሕግ ኃይል እና ውጤት የለውም እናም ሕዝቡን በምንም መልኩ ለማስገደድ የታሰበ አይደለም።

**ማስተባበያ፦**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

**የአገልግሎት ውል ናሙና**

ይህ የአገልግሎት ውል በ____________________ (“ቀጣሪ አካል”) እና __________________________ በ (የቤት ውስጥ ሠራተኛ”) መካከል ስምምነት የተደረሰበትን የቅጥር ውል፣ የሚቀርቡትን የቤት ውስጥ አገልግሎቶች የሚገልጽ የጽሑፍ ስምምነት ነው።

**1.** የቀጣሪ አካል ስም፡- __________________________________________

(a) የቀጣሪ አካል የንግድ አድራሻ፡- _____________________________________________

(b) የስልክ ቁጥር፡- ___________________________________________________

(c) የኢሜል አድራሻ፡- ___________________________________________

**2.** የቤት ውስጥ ሰራተኛ ስም፡- _____________________________________________

(a) የስልክ ቁጥር፡- ____________________________________________________

(b) የኢሜል አድራሻ፡- ___________________________________________

**3.** አብዛኛውን ጊዜ ሥራው የሚከናወንበት አድራሻ፡- __________________________________________________________ .

**4.** ***የስራ የመጀመሪያ ቀን።*** የቤት ውስጥ ሰራተኛው አገልግሎቱን መስጠት የሚጀምረው በሚከተለው ቀን ነው፡-______________________

**5.** ***የቅጥር ቆይታ ዘመን።***የዚህ ውል ጊዜ የሚጀምረው የቤት ውስጥ ሰራተኛው አገልግሎቱን መስጠት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሲሆን፣ የሚያበቃው፡- [አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ]፡-

☐ በሳምንታት ____________________ ውስጥ ☐ በወራት ውስጥ ☐ በዓመታት ውስጥ ☐ በክፍል 15 መሠረት ካልተቋረጠ በስተቀር፤

ወይም

☐ በ __________________ [ቀን ያስገቡ]፣ በክፍል 15 መሠረት ካልተቋረጠ በስተቀር።

**6.** ***አገልግሎቶች።*** የቤት ውስጥ ሰራተኛው በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩትን ከቤት ውስጥ ሰራተኛው የሚፈለጉ አገልግሎቶችን/ሃላፊነቶችን ይፈጽማል (የሚመለከታቸው ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ)፡-

☐ ልጆችን በቤት ውስጥ መንከባከብ፡-

☐ በዕድሜ የገፉ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች መርዳት፤

☐ ልብስ ማጠብና ዕቃ ማጠብን ጨምሮ ቤቱን ወይም በውስጡ ያለውን ነገር ማደራጀት፣ ማስተዳደር ወይም ማጽዳት፤

☐ ምግብ ማብሰል፣ ማዘጋጀት ወይም ማቅረብ፤ ወይም

**ማስተባበያ፡-**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

☐ ሌሎች ተግባራት፣ የሚከተሉትን ጨምሮ [ይግለጹ]:- ______________________________

______________________________

**አገልግሎቶችን የሚያገኙ ግለሰቦች:-**

| ስም | ዕድሜ | አገልግሎቶችን ስለሚያገኘው ግለሰብ ተጨማሪ መረጃ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

**7.** **ይህ የጋራ አገልግሎት ዝግጅት ሲሆን አንድ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች፣ ብዙውን ጊዜ በተመሳሳይ ጊዜ፣ ለ 2 ወይም ከዚያ በላይ ቀጣሪ አካላት የጋራ ጥቅም በመደበኛ የጊዜ ሰሌዳ ያከናውናል (ለምሳሌ፣ የሞግዚት መጋራት):-**

❑ አማራጭ 1:- አዎ፣ ይህ ዝግጅት በርካታ ቀጣሪ አካላትን ያካትታል። ቀጣሪ አካላት እና የቤት ውስጥ ሰራተኛ የዚህን ስምምነት ውሎች ለማብራራት ተጨማሪ መረጃዎችን ይጨምራሉ እና ሁሉም የሚመለከታቸው ቀጣሪ አካላት በስምምነቱ መጨረሻ ላይ ይፈርማሉ።

❑ አማራጭ 2:- አይ፣ ይህ ዝግጅት አንድ የቤት ሰራተኛን የሚቀጥር አንድ ቀታሪ አካልን ብቻ ያካትታል።

**8.** **በቤት ውስጥ መኖር።** ይህ በቤት ውስጥ ሰራተኛው ለሚሰጡት አገልግሎቶች በቤት ውስጥ መኖር የሥራ መደብ ነው? **አዎ** ☐ **አይደለም** ☐

**መልስዎ አዎ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ሁሉ ይግለጹ:-**

(a) የቀረበው የማረፊያ አይነት:- ______________________________

(b) የእንቅልፍ ጊዜ:- ______________________________

(c) የግል ጊዜ አመዳደብ:- ______________________________

**9.** **ክፍያ።** ቀጣሪው አካል ለተሰጡት አገልግሎቶች ለቤት ሰራተኛው ለመክፈል ይስማማል። ይህ ክፍያ በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ ይከፈላል:-

**የክፍያ መጠን:-** ______________________________

| | | |
|---|---|---|
| **በሰዓት?** | አዎ ☐ | አይ ☐ |
| **በቀን?** | አዎ ☐ | አይ ☐ |
| **በየሳምንት?** | አዎ ☐ | አይ ☐ |
| **በየሁለት ሳምንቱ?** | አዎ ☐ | አይ ☐ |
| **በየወሩ?** | አዎ ☐ | አይ ☐ |

**የትርፍ ሰዓት ክፍያ በሰዓት*:-** ____________________ በሳምንት ከ40 ሰዓት በላይ ለሚሠራው እያንዳንዱ ሰዓት (ወይም የእያንዳንዱ ሰዓት ክፍልፋይ)

**የክፍያ አይነት:-** **ቼክ?** አዎ ☐ አይ ☐ **በጥሬ ገንዘብ?** አዎ ☐ አይ ☐ **ቀጥተኛ ተቀማጭ ገንዘብ?** አዎ ☐ አይ ☐

**የክፍያ ድግግሞሽ:-**

☐ በየሳምንቱ ______________ (የሳምንቱ ቀን) ላይ

ማስተባበያ:-ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

☐ በየሁለት ሳምንቱ ______________ (የሳምንቱ ቀን) ላይ በየሁለት ሳምንቱ

☐ በየወሩ ___________________ (የወሩ ቀን) ላይ

☐ ሌላ:- ___________________________

**የመጀመሪያው የደመወዝ ክፍያ ለቤት ውስጥ ሰራተኛው የሚከፈልበት ቀን:-** _____________________________________

10. **ሳምንታዊ መርሐ ግብር:-** እባክዎ የቤት ውስጥ ሰራተኛውን ሳምንታዊ መርሐ ግብር ያመልክቱ:-

**የስራ ቀናት**:- እሁድ ☐ ሰኞ ☐ ማክሰኞ ☐ ረቡዕ ☐ ሐሙስ ☐ አርብ ☐ ቅዳሜ ☐

**መጀመሪያ ሰዓት:-** _______ AM ☐ PM ☐ **መጨረሻ ሰዓት:-** ______ AM ☐ PM ☐ **በሳምንት ጠቅላላ የሚሰሩ ሰዓቶች:-** ___

**የምግብ እረፍት:-** No ☐ Yes ☐ የሚጀምርበት ጊዜ:- _ AM ☐ PM ☐ የሚያበቃበት ጊዜ:- _ AM ☐ PM ☐

**የእረፍት ጊዜ:-** አይ ☐ አዎ ☐ የሚጀምርበት ጊዜ:- ____ AM ☐ PM ☐ የሚያበቃበት ጊዜ:- _ AM ☐ PM ☐

**የእረፍት ጊዜ:-** አይ ☐ አዎ ☐ የሚጀምርበት ጊዜ:-_____ AM ☐ PM ☐ የሚያበቃበት ጊዜ:- _ AM ☐ PM ☐

11. **የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ:-** ለቤት ውስጥ ሰራተኛው የሚሰጠውን የሥራ ፈቃድ መጠን እና ዓይነት እንዲሁም የሚከፈልበት ወይም የማይከፈልበት መሆኑን ያመልክቱ።

☐ **የሕመም እና የደህንነት ፈቃድ:-** ማካካሻ (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ):- ☐ የሚከፈልበት ወይም ☐ የማይከፈልበት
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ለ _______________ ሰዓታት ሥራ _______________________ ሰዓታት የሕመም ፈቃድ፣ እስከ ___ ቀናት በቀን መቁጠሪያ ዓመት ያገኛል።
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ በየዓመቱ በዓመቱ ውስጥ ሊጠቀምባቸው ከሚችላቸው _______ ሰዓታት የሕመም ፈቃድ ጋር ይጀምራል።

☐ **የእረፍት ፈቃድ:-** ማካካሻ (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ):- ☐ የሚከፈልበት ወይም ☐ የማይከፈልበት
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ለ _______________ ሰዓታት ሥራ ____________________________ ሰዓታት የእረፍት ፈቃድ፣ እስከ ___ ቀናት በቀን መቁጠሪያ ዓመት ያገኛል።
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ በየዓመቱ በዓመቱ ውስጥ ሊጠቀምባቸው ከሚችላቸው _______ሰዓታት የእረፍት ፈቃድ ጋር ይጀምራል።
☐ የቤት ሰራተኛው የእረፍት ጊዜውን ለመጠቀም ፍላጎት እንዳለው ከ ________________________________ ቀናት በፊት ለቀጣሪው አካል ማሳወቅ አለበት።

☐ **የሚከፈልበት የቤተሰብ ዕረፍት:-** ማካካሻ (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ):- ☐ የሚከፈልበት ወይም ☐ የማይከፈልበት
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ በቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ __ ቀናት ያገኛል።
☐ የቤት ውስጥ ሰራተኛ በየዓመቱ በዓመቱ ውስጥ ሊጠቀምባቸው ከሚችላቸው _______ሰዓታት የሚከፈልበት የቤተሰብ እረፍት ጋር ይጀምራል።

☐ **ሌላ** ______________ : ማካካሻ (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ):- ☐ የሚከፈልበት ወይም ☐ የማይከፈልበት
የእረፍት ጊዜ መጠን:- __________________________________
የእረፍት ጊዜው ለምን አላማ ሊውል እንደሚችል:- ________________________________

☐ ቀጣሪው አካል የሚከተሉትን የዕረፍት ጊዜያት ይሰጣል፣ ይህም ☐ የሚከፈልበት ወይም ☐ የማይከፈልበት ይሆናል
____________________________________________________________________________________________
__________________________________________________________________________________________

12. **የሥራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት**
1. ከትባቶችን ጨምሮ በኮቪድ-19 እና በሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ፕሮቶኮሎች ዙሪያ የሚጠበቁ ነገሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-
_________________________________________________________________________________________
_________________________________________________________________________________________
______________________________________________

**ማስተባበያ:-**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

2. ቀጣሪው አካል የቤት ውስጥ ሰራተኛው በሥራው ላይ ጉዳት ቢደርስበት ወይም ቢታመም የሚመለከተው ህግ በሚጠይቀው መሰረት የደመወዝ ማጣት እና የህክምና ጥቅማጥቅሞችን ለመሸፈን የሚያስችል የሠራተኞች የጉዳት ካሳ ወይም ተመጣጣኝ ካሳ (ለምሳሌ፥ በራስ ኢንሹራንስ ወይም በቤት ባለቤት ኢንሹራንስ) ያቀርባል (አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ)፡- ☐ አዎ (የኢንሹራንስ ዝርዝሮች፡- ________) ወይም ☐ አይ

**13.** **የቀጣሪ አካል የቤት ውስጥ ሰራተኛ ተጨማሪ ማካካሻ ወይም ክፍያ።** እባክዎ የጤና ኢንሹራንስ ክፍያዎች፣ የትራንስፖርት አበል ወይም የመለያያ ክፍያ የመሳሰሉ ከቀጣሪው የሚከፈሉ ማናቸውንም ማካካሻዎች ወይም ክፍያዎች ይዘርዝሩ።

______________________________________________________________________________

**14.** **የትራንስፖርት መስፈርት፡-** የቤት ውስጥ ሰራተኛው የስራ ግዴታውን ለመወጣት የራሱን ተሽከርካሪ ማቅረብ ካለበት እባክዎ ያመልክቱ። አዎ ☐ አይ ☐።

ምላሹ አዎ ከሆነ፣ የቤት ውስጥ ሰራተኛው ለነዳጅ ውጪው ይከፈለዋል? አዎ ☐ አይ ☐ በምን መጠን?________________________

**15.** **ማቋረጥ።**

(a) ከሁለቱም ወገኖች አንዱ ሌላኛውን ወገን በ ________________________________ ቀናት በጽሑፍ አስቀድሞ በማሳወቅ በማንኛውም ጊዜ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል። ቀጣሪው አካል የውል ስምምነቱን የሚያቋርጥ ከሆነ፣ አሰሪው የቤት ውስጥ ሰራተኛው እስከ ማቋረጡ ቀን ድረስ ላከናወናቸው አገልግሎቶች እና ከማቋረጡ ቀን በፊት የተፈቀዱ ነገር ግን ያልተከፈሉ ወጪዎችን ሁሉ የመክፈል ግዴታ አለበት። የቤት ውስጥ ሰራተኛው የውል ስምምነቱን የሚያቋርጥ ከሆነ፣ ለቤት ውስጥ ሰራተኛው ቀደም ሲል የተከፈሉ እና የቤት ውስጥ ሰራተኛው ገና አገልግሎት ያላከናወነባቸውን የገንዘብ መጠኖች ለቀጣሪው አካል ይመልሳል።

(b) ይህ ውል ሁለቱም ወገኖች በውል የተጣለባቸውን ግዴታዎች በሙሉ ሲፈጽሙና ሁሉም ክፍያዎች ክፍያ እንደተፈፀመ ወዲያውኑ ያበቃል።

**ማስተባበያ፡-**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

**16.** ***የሁለቱ ወገኖች ግንኙነት።***

(a) **ላንድ ወገን ብቻ ተፈፃሚ የሚሆን ነገር የለም።** ሁለቱም ወገኖች ይህ ውል ብቸኛ ስምምነት አለመሆኑን ይገነዘባሉ። ሁለቱም ወገኖች ከሌሎች ወገኖች ጋር ሌሎች ተመሳሳይ ስምምነቶችን ለመፈጸም ነፃነት እንዳላቸው ይስማማሉ። የቤት ውስጥ ሰራተኛው በዚህ ውል መሰረት ከቤት ውስጥ ሰራተኛው ግዴታዎች ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ውል እንደማይፈፅም ተስማምቷል።

**17.** ***ግብርና የደመወዝ ክፍያ ተቀናሾች***

(a) ቀጣሪው አካል የማኅበራዊ ዋስትና እና የ Medicare ግብርን ጨምሮ በሕግ የሚጠየቁትን የአካባቢ፣ የስቴት እና የፌዴራል ግብሮችን ይከፍላል እንዲሁም ይይዛል እንዲሁም ሌሎች በሕግ የሚጠየቁትን ሁሉ ይቀንሳል።

(b) በቤት ውስጥ ሰራተኛው መመሪያ መሰረት ቀጣሪው አካል የቤት ሰራተኛውን የገቢ ግብር በመያዝ______(በመጠን ወይም በመቶኛ) ይቆጥባል።

(c) ከቤት ውስጥ ሰራተኛ ደመወዝ የሚወሰዱ ማናቸውም ተጨማሪ ቅናሾች በጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው እና የምግብ፣ መጠጥ እና ማረፊያ ቅናሾችን የሚቆጣጠረውን የፍትሃዊ የሠራተኛ ደረጃዎች ሕግ ክፍል 3(m)ን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የስቴት እና የአካባቢ ሕጎች ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው። የሚከተሉት ቅናሾች በ

______________________ (የክፍያ ጊዜ/ወር) ይደረጋሉ፡-

ሀ. ለጤና ኢንሹራንስ የሚቀነስ መጠን፣ ተፈፃሚነት ካለው: $ ____________________

ለ. ለምግብ እና ለመጠጥ የሚቀነስ መጠን፣ ተፈፃሚነት ካለው፡- $____________________

ሐ. ለማረፊያ/ለማደሪያ የሚቀነስ መጠን፣ ተፈፃሚነት ካለው፡- $ _________________________

መ. ለሌሎች ተቀናሾች የሚቀነስ መጠን፣ ተፈፃሚነት ካለው፡- $______________________

**ማስተባበያ፡-**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።

ተዋዋይ ወገኖች ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ውሎች እና ሁኔታዎች ተስማምተዋል፣ ይህም በፊርማዎቻቸው እንደሚከተለው ተረጋግጧል፦

**ቀጣሪ አካል**

ፊርማ፦ ______________________________

የጽሑፍ ስም፦ ______________________________

የተፈረመት ቀን፦ ______________________________

**የቤት ውስጥ ሰራተኛ**

ፊርማ፦ ______________________________

የጽሑፍ ስም፦ ______________________________

የተፈረመት ቀን፦ ______________________________

**ማስተባበያ፦**ይህ የአገልግሎት ውል ናሙና የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ማንኛውንም የሕግ ግዴታ የሚያንፀባርቅ አይደለም እንዲሁም የሕግ ምክር አይሆንም።